

ዶ/ር አበበች ጎበና
1928 – 2013 ዓ.ም
“ህፃናትን በምንም ነገር አልተምንም፡፡”



“እራሴ የወለድኳቸው ልጆች የሉኝም፤ ግን በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ልጆች እንዲሁም ቤተሰብ አፍርቻለሁ ስለዚህ ምንም አይቆጨኝም።”

# ዶ/ር አበበች ጎበና: የብዙሀን እናት



ዶ/ር አበበች ጐበና ከአባታቸው ከአቶ ጎፌ ሄዪ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ወሰኔ ብሩ ጥቅምት 10 ቀን 1928 ዓም በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት፤ በሰሜን ሸዋ ዞን፤ በግራር ጃርሶ ወረዳ፤ ቶርበን አሸ ቀበሌ ልዩ ስሙ ሸበል በሚባል ቦታ ተወለዱ። አባታቸው አቶ ጎፌ ሄዪ ገና በተወለዱ በዓመታቸው በጣልያን ወራሪ ሃይል ስለተገደሉባቸው ወንድ አያታቸው አቶ ሄዪ በዲሴ ወሰደዋቸው በአያታቸው ቤት አደጉ። ዕድሜያቸው አሥር አንድ ዓመት እንደደረሰ በአካባቢው ወግና ባህል መሠረት እናታቸው ወስደው ዳሯቸው።

ያለፈቃዳቸው የተደረገውን ጋብቻ ጠልተው ብዙ ሳይቆዩ ለመልስ እናታቸው ቤት ተጠርተው የተፈጠረውን አጋጣሚ በመጠቀም ጠፍተው እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታን በማሳለፍ አዲስ አበባ ገቡ። አዲስ አበባ ገብተው በተለያዩ ድርጅቶችና ካንፓኒዎች በመሥራት የግል ንግዳቸውን በማንቀሳቀስ ኑሮአቸውን ሲመሩ ቆይተው የተረጋጋ ሁኔታ ሲፈጠር ሚያዚያ 27 ቀን 1953 ዓ.ም ከአቶ ከበደ ኮስተር ጋር ተጋብተው ከሃያ ዓመት በላይ የተደላደለ ሰላማዊ ኑሮ መርተዋል።

በዚህ ጊዜ ከግል ህይወታቸው ባሻገር ማህበራዊ ግንኙነታቸውን እና ተሳትፎአቸውንም አስፍተው አስተዋጽኦ ያደረጉ ሲሆን ህይማኖታዊ ግዳጃቸውንም ለመወጣት ገዳማትን በመጐብኘትና በዚያ የሚኖሩ አባቶችንም በመርዳት ይተጉ ነበር፡፡ ወደ ግሸን ማሪያም የሚወስደውንም መንገድ ለማሠራት በተቋቋመው ኮሚቴም በመሳተፍ ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከታቸው ከተሰጣቸው ምስክር ወረቀት መረዳት ይቻላል፡፡

በ1972 ዓ.ም የግሸን ማሪያም ዓመታዊ ክብረ በዓልን ለማክበር ወደሥፍራው በሚሄዱበት ወቅት በወቅቱ በሃገራችን ከፍተኛ የድርቅና የረሃብ አደጋ ተከስቶ ብዙ ሰዎች በአደጋው ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው በየመጠለያው ይገኙ ስለነበር እነዚያን መጠለያዎች ሲጎበኙ ባዩት አሰቃቂ ሁኔታና ሕፃናት ያለተንከባካቢ ቀርተው በማግኘታቸው ሁለት ሕፃናትን ወደ አዲስ አበባ ይዘው በመምጣት የዛሬውን "አበበች ጐበና የሕፃናት ክብካቤና ልማት ማህበር" ለማቋቋም መሠረት ጣሉ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሞቀ ትዳራቸውን በመተው የጀመሩትን ሕፃናትን የመንከባከብ እና የሰብዓዊ አገልግሎት ተግባርን በመቀጠል ላለፉት 41 ዓመታት ብዙ መቶ ሺህ ህፃናትን ትንከባክበው ለቁምነገር ያበቁ ሲሆን በተለያዩ ድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞች ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ለአብነትም፡-

1. የብዙ መቶ ሺህ ህፃናትን ህይወት ታድገው ለቁም ነገር አድርሰዋል፡፡
2. የበርካታ ሺህ ሴቶች ኑሮ እንዲሻሻልና ልጆቻቸውን በአግባቡ እንዲንከባከቡ አስችለዋል፡፡
3. የሴቶችን አቅም ለመገንባት የሙያ ማሰልጠኛ ከፍተው በማሰልጠን በሺዎች የሚቆጠሩ ችግረኛ ሴቶችን ለስራ አብቅተዋል፡፡
4. በማህበሩ በቡራዩ እና በአዲስ አበባ ሁለት መደበኛ ትምህርት ቤቶችን አስገንብተው የውስጥ ቁስቁሶችን በሟሟላት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ እና የትምህርት ዕድል ላጡ ህፃናት መማሪያ በማድረግ ብዙዎችን ለከፍተኛ ኃላፊነት እንዲበቁ አስችለዋል፡፡



የዶ/ር አበበች ጎበና የመጀመሪያዎች ልጆች

5. በአዲስ አበባና ኦሮሚያ ለሚገኙ ብዙ ሺህ ቤቶች የብድርና ቁጠባ አገልግሎቶች እንዲያገኙ ረድተዋል፡፡
6. የአካባቢ ጥበቃን ለማጠናከር በየአመቱ ከ100 ሺህ በላይ ችግኞችን በማፍላትና በማሰራጨት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡
7. የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ለአብነት ባህላዊ የምግብ ዝግጅት፣ ሹራብ ስራ፣ የምግብ ዘይት ምርት፣ የልብስ ህትመት፣ የቅርቃሃ ምርት፣ ልብስ ስፌት፣ የጥልፍ ስራ፣ የስጋጃ ስራ፣ የሽመና ስራ፣ ዶሮ እርባታ፣ ከብት እርባታ፣ የወተት ተዋፅኦ ሽያች፣ የጓሮ አትክልት፣ የወፍጮ አገልግሎት፣ የማር ጠጅ ዝግጅት፣ ባህላዊ አልባሳት እና ስጦታ እቃዎች እንዲሰሩ በማድረግ ተቋማቸውን አጠናክረዋል፡፡
8. የምግብ እህል፣ አልባሳት፣ የምርት ዘር ኦሮሚያና አዲስ አበባ ለሚገኙ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አባወራዎች እንዲያገኙ አድርገዋል፡፡
9. ከ50 በላይ ውሃ ቦኖዎችን፣ ምንጭ በማጎልበት እና በእጅ የተቆፈሩ የውሃ ጉድጓዶችን አሰርተው ለአገልግሎት አብቅተዋል፡፡
10. ከሌሎች በጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር በመሆን በርካታ የህዝብና የመንግስት ትምህርት ቤቶችን፣ የጎልማሶች ትምህርት ማእከላትን፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ሜዳዎችን፣ አጥሮችን፣ አስገን-ብተው ለተጠቃሚ አስተላለፈዋል፡፡
11. በኦሮሚያ ክልል 27 መደበኛ ያልሆኑ ትምህርት ቤቶችን ገንብተው የሰው ሀይልና ቁሳቁሶችን አሟልተው ለ3 ዓመታት የመማር ማስተማር ካከናወኑ በኋላ ለመንግስት አስረክበዋል፡፡
12. የቴ/ሙ/ስልጠና ተቋም በፍቼ ከተማ አስገንብተው ለተጠቃሚዎች አስተላልፈዋል፡፡
13. ከ350 በላይ የችግረኛ አባወራ ቤቶችን በማስጠገን ለተጠቃሚዎች አስረክበዋል፡፡
14. ከ350 በላይ ኩሽና ቤቶችን፣ የገበያ ሱቆችንና መፀዳጃ ቤቶችን በማሰራት ለአገልግሎት አብቅተዋል፡፡
15. የህፃናትን ጉስቁልና እና የእናቶችን በወሊድ ሳቢያ የሚከሰት ሞት ለመቀነስ አንድ ልዩ የእናቶችና የህፃናት ሆስፒታል ገንብተዋል፡፡
16. በወሎ፣ በሰሜን ሸዋ፣ በድሬዳዋ፣ በደቡብ ኦሞ እና በሌሎች በርካታ የተፈጥሮ አደጋዎች ለተጎዱ ወገኖች ድጋፍ አድርገዋል፡፡
17. የረሀብን ማብቂያ በአእምሯቸው እያሰቡ የመስኖ ግድብ አስገንብተው በሺዎች ለሚቆጠሩ ቤተሰቦች የምግብ ዋስትናን አረጋግጠዋል፡፡
18. በሀገራችን በኤች አይ ቪ/ኤድስ የተያዙ ሰዎች ላይ ከፍተኛ መድሎና መገለል በሰፈነበት እንዲሁም የማህበረሰብ ግንዛቤ ውስን በነበረበት ወቅት የግንዘቤ ማሰጨበጫ ስራዎችን በመስራት አመርቂ ለውጥ አምጥተዋል፡፡
19. በኤች አይ ቪ/ኤድስ ለተጎዱና እጅግ ለችግር ለተጋለጡ ብዙ ቤተሰቦች የእንክብካቤና የህክምና፣ የቁሳቁስ፣ የገንዘብ፣ የመኖሪያ ቤት እና የመሳሳሉት ድጋፍ አድርገዋል፡፡

20. በሰሩባቸው አከባቢዎች የቤተሰብ ምጣኔና ስነ-ተዋልዶ ጤና ትምህርት በመስጠት፣ ማህበረሰብ ዘንድ የባህሪ ለውጥ እንዲመጣ በማድረግ የቤተሰብ ምጣኔና ስነ-ተዋልዶ ጤና አግልግሎት ሽፋን በጣም ከፍ እንዲል አድርገዋል፡፡
21. በአዲስ አበባና በኦሮሚያ፣ በመስራተ ልማት ግንባታ፣ በአቅም ግንባታ፣ በጤናና የቤተሰብ ምጣኔ፣ በትምህርት፣ በግብርና ልማታዊ አስተዋፅዖዎችን በስፋት ሰርተዋል፡፡




ዶ/ር አበበች ጐበና (እዳዬ) በህይወት ዘመናቸው ላበረከቱት አርአያነት ያለው አኩሪ ሥራ የሰብዓዊነትና የሴቶች ህያው አርአያ የበጐ ተግባር ከተለያዩ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት ታላላቅ ሽልማቶችንና እውቅናዎችን አግኝተዋል፡፡ ከሽልማቶቹም መካከል፡-

- ከጅማ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ በሂውማኒቲ
- ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሜዳሊያ እና የክብር የምስክር ወረቀት
- በሁለተኛው የዓለም ምግብ ፕሮግራም ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን የክብር ተሸላሚ
- ከተባበሩት መንግስታት የኢትዮጵያ ማህበር፣ ከቤተሰብ ፌዴሬሽን ለዓለም ሰላም እና ከተባበሩት መንግስታት የበጎ ፈቃደኞች ፕሮግራም ዋንጫ እና የምስክር ወረቀት
- በ CCRDA የብር እዮቤልዩ ክብረ በዓል ላበረከቱት ከፍተኛ አስተዋፅዖ የእውቅና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት
- ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስትያን የክብር የምስክር ወረቀት እና ዋንጫ
- ከኢትዮጵያ አየር መንገድ የክብር የምስክር ወረቀት፣ ሜዳሊያና ዋንጫ
- ከኢንተር ሪሊጅየስ ኤንድ ኢንተርናሽናል ፌዴሬሽን ፎር ዎርልድ ፒስ የሠላም አምባሳደርነት የምስክር ወረቀት

- ሰብአዊ ርዳታን በመደገፍ የቡድን ስፔን ሽልማት
- ከሴቶች ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች አበረታች ማእከል የምስክር ወረቀት
- ለአፍሪካ ዘላቂ ልማት ፋይዳ ላለው አርአያነትና ተነሳሽነት ሥራቸው የማዕከላዊ አፍሪካ የክልል አሸናፊ በመሆን የምስክር ወረቀት እና ዋንጫ
- ዓለም አቀፍ ሽልማት" ከለንደን ወርልድዌር ቢዝነስ አዋርድ"
- በአፍሪካ ደረጃ ማ. አፍሪካ (እናት አፍሪካ) ከደቡብ አፍሪካ
- ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በተለያዩ ጊዜያት ዋንጫዎችና ምስክር ወረቀቶች
- ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ከንቲባ ጽ/ቤት በተለያዩ ጊዜያት ልዩልዩ ሽልማቶች
- ከተለያዩ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የማበረታቻ እና እውቅና ሽልማቶች
- ከተለያዩ አለም አቀፍ ድርጅቶች ልዩ ልዩ የማበረታቻ እውቅናና ሽልማቶች በዋናነት የሚጠቀሱ ሲሆን ሌሎች ከመቶ በላይ እጅግ በርካታ ሽልማቶችንም አግኝተዋል፡፡



















ዶ/ር አበበች ጉበና ለህዝብ ላበረከቱት የላቀ አስተዋፅኦ በርካታ ተቋማት በስማቸው ተሰይመዋል፡፡ ለአብነትም፡-

- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሀገራችን የመጀመሪያ የሆነው አበበች ጉበና የእናቶችና ህፃናት ሆስፒታል፣
- በሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አበበች ጎበና ካምፓስ፣
- በአምቦ ዩኒቨርሲቲ አበበች ጎበና ግብርና ምርምር ማዕከል፣
- በአዲስ አበባ ሁለት የግል ባንኮችና አንድ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡




ክብርት ዶ/ር አበበች (እዳዬ) "ድህነትን በተለይም የህፃናት ጉስቁልናን መቅረፍ የሚቻለው በግለሰብ ደረጃ ለምፅዋት በሚወረወሩ ሽርፍራፊ ሳንቲሞች ሳይሆን በአንድነት በማበር እና ያለንን አቅም በማሰባሰብ በችግር ላይ ያሉ ወገኖቻችንን በተለይም ሴቶችን ስናበቃ ነው፡፡" የሚል እምነት ነበራቸው፡፡

ዶ/ር አበበች ጉበና (እዳዬ) ላለፉት 41 ዓመታት ማህበሩን በመምራት ባሳለፉት እጅግ ፈታኝ ጫና የበዛበት የሥራ ዘመን ምክንያት የጤና ችግር እየገጠማቸው በተደጋጋሚ ቀዶ ጥገና የተደረገላቸው ሲሆን ከ16 ዓመት በላይ በልባቸው ላይ በተገጠመ መሣሪያ /pacemaker/ አማካይነት ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል፡፡

ከተወሰኑ ጊዜያት ወዲህ የጤና ችግር ከዕድሜ መግፋት ጋር ተዳምሮ ባስከተለው ችግር ምክንያት በመኖሪያ ቤታቸው ሆነው የሃኪም ክትትልና ዕርዳታ ሳይለያቸው እንክብካቤ ሲደረግላቸው ቆይቷል፡፡



ሆኖም በቅርቡ በኮሮና በሽታ ምክንያት በጳውሎስ ሆስፒታል በጽኑ ህሙማን ክፍል ሲረዱ ቆይተው ሰኔ 27/2013 በተወለዱ በ85 ዓመታቸው ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል፡፡

የእኝህ ደግ እና ሩህሩህ እናት ስራ ከመቃብር በላይ ገኖ ለዘላላም በአርአያነት በትውልድ ሲታወስ ይኖራል፡፡

ለዘመድ አዝማዶቻቸው፤ ያለ እርሳቸው አለኝታ ላልነበራቸው ታዳጊ ሕፃናትና ልጆቻቸው ለዓላማቸው ደጋፊዎች እንዲሁም አጋሮች መጽናናትን እንመኛለን፡፡


የደጓ እናታችንን ነብስ ፈጣሪ በአፀደ ገነት ያኑርልን፡፡ አሜን፡፡

**ዘላለማዊ ክብር ለክብርት ዶ/ር አበበች ጎበና!**

**ሰኔ 2013 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**







This is to certify that

Abebech Gobena - Ethiopia

participated in the international finals of


MáAFRIKA
2002

Her inspiring work in the interest of sustainable development within her community was highly commended by the adjudicators.

CHAIRPERSON

Ekurhuleni, 8 March 2003




Awarded to

Abebech Gobena - Ethiopia

Regional Winner Central Africa

MáAFRIKA
2002

For her truly exemplary and inspirational work in the interest of sustainable development for Africa.

CHAIRPERSON

Ekurhuleni, 8 March 2003

# ከዶ/ር አበበች ጎበና ትላልቅ
# ዓለም አቀፍ ሽልማቶች ጥቅቶቹ



Menschen für Menschen
Karlheinz Böhms Äthiopienhilfe Switzerland

የህይወት ታሪካቸውን ጽሁፍ እንድናዘጋጅ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልን ለሠዎች ለሠዎች ስዊዘርላንድ እና አጠቃላይ የቀበር ስነ-ስርዓቱን ላቀናጀው ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም ድጋፍ ላደረጉልን አጋሮቻችን ሁሉ ምስጋና እናቀርባለን፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ በቂ የጤና ባለሙያዎችን በመመደብ እናታችንን ለማዳን ላደረገው ከፍተኛ ርብርብ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን፡፡

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
Addis Ababa City Administration

# አፍሪካዊቷ ማዘር ቴሬዛ



## አበበች ጎበና

**አበበች ጎበና የሕፃናት ክብካቤና ልማት ማህበር (አጎሕልማ)**


☎ +251 118 694 629

Fax: +251 111 550 152

✉ 24998 Addis Ababa, Ethiopia

E-mail: info@agohelma.org

Website: http://www.agohelma.org